Coptic Orthodox Patriarchate
His Holiness Pope Tawadros II
Pope of Alexandria and
Patriarch of the See of St. Mark
The Papal Center

بطريركية الأقباط الأرثوذكس
قداسة البابا الأنبا تواضروس الثاني
بابا الأسكندرية
وبطريرك الكرازة المرقسية
المقر البابوي

Ⲑⲁⲟⲩⲁⲇⲣⲟⲥ

222 Ramses St., Abbaseya, Cairo, Egypt
222 شارع رمسيس ، العباسية ، القاهرة ، مصر
Tel: 024822580 Fax: 0235365880 email: office@popetawadros.org فاكس: 0235365880 تليفون: 024822580

*Amharic*

## የልደት በዓልን በማስመልከት ቅዱስ ፓትርያርኩ ያስተላለፉት ቃለ በረከት

### በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

በአዲሱ ዓመት በ2019 መጀመሪያ ላይ ሆኘ እንኳን ለጌታ የልደት በዓል አደረሳችሁ እላችኋለሁ። መልካሙን ሁሉ እና በረከቱን ሁሉ እመኝላችኋለሁ። ልባዊ ሰላምታየን እንዲሁም የሁሉንም ግብጽ ውስጥ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ሰላምታ አቀርብላችኋለሁ፡ ይህም ለሁሉም ሜትሮጶሊታን እና ጳጳሳት፣ ለሁሉም ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ አገልጋዮች፣ ተመራጨች፣ የቤተ ክርስቲያን ቦርድ አባላት፣ ወጣቱ፣ በተጨማሪም ሁሉም ማኅበራት እና ሁሉም ልጆች እና በዓለም ላይ ባሉ በሁሉም አህጉራት ለሚገኙ ኮፕቲክ አብያተ-ክርስቲያናት ሁሉ፡- ሰሜን አሜሪካ፣ ደቡብ አሜሪካ፣ አውሮፓ፣ አፍሪካ፣ እስያ እና አውስትራሊያ፤ በሁሉም ስፍራ ከሚገኙ ሁሉ ጋር በምሥራቃዊ የቀን መቁጠሪያ መሠረት ታላቁን የልደት በዓል ለሚያከብሩ።

እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረው በኋላ ፍጹም ሰብዓዊ ፍጡር ሆኖ የሚኖር ፍጹም ሰው እንዲሆን ፈልጎ ብዙ ሥጦታን ሰጥቶታል። ሆኖም ግን ሰው ኃጢአትን መረጠ፤ የእግዚአብሔርንም ትእዛዝ አፈረሰ፤ በጨለማም ኖረ። ይህን ሰው የኖረበትን ጨለማ "መንፈሳዊ ጨለማ" እንለዋለን። በነፃነት፣ ፍቅር እና የእግዚአብሔር ሥርዓት ደስ እንዲሰኝ ከተፈጠረ በኋላ ሰው በሥራ ፈትነት፣ በተስፋ መቁረጥ እና በኃጢአት ውስጥ ለመኖር መረጠ። ይህም ተስፋ የጠፋበት እና የሚያስፈራ ነበር። ከዚያ ኃጢአት ተስፋፍቶ ወደ መላው ዓለም ተንሰራፋ። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈው "ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል" (ሮሜ 3:23) እናም በሰዉ ውድቀት ፍጥረት በጣም አስፈላጊ የሆነውን ነገር አጣ፣ የሰው ዘርን። በጣም በቀስታ፣ በትውልዶች ሂደት በሰው ዘር ውስጥ የተዘራው ፍቅር ደረቀ፤ ይህም ሰዎች ፍቅርን እንዲራቡ ያደረጋቸውን ክፍተት ተወ። ምንም እንኳን በመላው ዓለም ውስጥ በመገናኛ መንገዶች ላይ ትልቅ እድገት ቢኖርም ይህ የፍቅር ረሃብ ሰውን በከባድ ባዶነት እንዲኖር አደረገው።

መፍትሔው ምንድን ነው?

መፍትሔው ፍቅር ነበር:: አንድ አካል ከራሱ ፍቅር የተነሳ መጥቶ ፍቅርን እንደገና ወደ ቀድሞ ሁኔታው መመለስ ይገባው ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደምናነበው ጌታችን እና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን ተዋሐደ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" (ዮሐ. 3 16)። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የዋህነትን፣ ደግነትን እና ፍቅርን ለመስጠት መጣ። የእርሱ ዓላማ ሰውን እንደገና ወደ ሰውነቱ ለመመለስ ነበር። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከመሆኑ የሚልቅ ሌላ መንገድ ሊኖር አይችልም ነበር። ስለዚህ አማኑኤል "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" ሆነ። ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በመካከላችንም አደረ።

እግዚአብሔር መልአክ ወይም የመላእክት አለቃ ወይም ነቢይ አልላከም። ወይም ፖለቲከኛ ወይም አምባሳደር አይደለም፤ ነገር ግን እራሱ መጣ። የመጣው እግዚአብሔር ሰውን በእውነት ስለሚወደው ነው፣ በቃላት ሳይሆን በድርጊት። ስለዚህ በየዓመቱ የልደትን በዓል እናከብራለን። እናም ይህ አጋጣሚ ታድሷል። ከፍቅሩ የተነሳ ፍቅር ከሰጠን ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ቃል ኪዳን እናድሳለን። በክቡር ልደቱ ውስጥ ትንሿን ቤተልሔምን ሲወዳት እናያለን። ታላቁን የኢየሩሳሌምን ከተማም ይወድዳል። በተጣበበው ዓለም መካከል የተረሱ እረኞችን ሲወድ እናያለን፤ በዚያኑ ጊዜ ደግሞ ጠቢባንን ሰብአ ሰገልን ሲወድ እናያለን። ከይሁዳና ከኢየሩሳሌም ርቀው በሩቅ ይኖሩ የነበሩትን። ድሆችንና ወላጅ የሌላቸውን ልጆች ይወድዳል፤ እንዲሁም ባሏ የሞተባትን ሴት ነብይት ሃናንም ይወዳል። የሥጋዌውን ምሥጢር የጠበቀውን ጻድቁን ሽማግሌ አናጢውን ዮሴፍን ይወደዋል። እንዲሁም የክርስቶስን መምጣት ሲጠብቅ የነበረውን ታላቁን ሽማግሌ ስምዖንን ይወደዋል። እግዚአብሔር የሰው ልጆችን በሙሉ ይወድዳልና አሁን ከጠፋባቸው ፍቅር ሊያረካቸው መጣ። ሰው ሰውነቱ እንደገና እንዲታደስ ይህ ፍቅር ያስፈልገው ነበር።

ስለዚህ በዚህ ታላቅ የልደት በዓል ውስጥ እግዚአብሔር ለእናንተና ለሁሉም ፍጥረታቱ ፍቅሩን ይልካል። ይህንን ፍቅር ይልክላችሁና እግዚአብሔር ከእናንተ ሩቅ እንዳልሆነ ይነግራችኋል። እግዚአብሔር እናንተን "ፈጽሞ አልረሳችሁም" ይላችኋል። እግዚአብሔር "ሰውን አልጠላም" ይላችኋል። ይልቁንስ የሰውን ኀጢአት ይጠላል፤ ሰው ራሱን ግን ይወዳል። እርሱ ሁሉንም ፍጥረታት ይፈልጋል፤ እርሱ የመጣው በተስፋ እና በደስታ እንድትሞሉ እና የእልልታ ድምጽ ሊሰጣችሁ ነው። እግዚአብሔር ሰውን በፍቅሩ ወደ ሰውነቱ ይመልሳል።

ስለዚህ በሁሉም ቦታ ያላችሁ የተወደዳችሁ ሆይ፤ በልባችሁ ውስጥ ያለውን ፍቅር ምንም ነገር እንዳይቀንሰው ተጠንቀቁ። ክርስቶስ በሚሰጣችሁ ፍቅር ልባችሁ ሁልጊዜም እንደሞቀ ልብ በሉ። የምንታገላቸው ወቅታዊ ሁኔታዎች እና በመላው ዓለም የሚገኙት ሰፊ የመገናኛ ዘዴዎች በአነስተኛ መንደር ውስጥ የምንኖር እንደሚያስመስሉን እወቁ። ተደጋጋሚ ከሆነው የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች አጠቃቀሙ የተነሳ በሰው ልብ ውስጥ ያለው ፍቅር ደረቀ፤ ብዙ ድክመቶች በሰው ፊት ጨመሩ። ከሌሎች ጋር ባለው ግንኙነት፣ ለሰዎች ባለው ፍቅርና ለህይወቱ ባለው ፍቅር ሁሉ ድክመት ጨመረበት። ዓለም በአመጽ፣ በወንጀል፣ በአሸባሪነት እየጨመረ እናገኘዋለን። የቤተሰብ ደካማነት እና በተለያዩ ልቅነቶች እየበዙ ሄዱ። ይህ ሁሉ የተከሰተው በሰው ልብ ውስጥ ፍቅር ባለመኖሩ ነው።መጥተን በዚህ ፍቅር እንድንሞላ የልደት በዓል ለእያንዳንዳችን እድል እና መልዕክት ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ ላይ እንደተናገረው "ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው እነርሱ ይጠግባሉና" (ማቴዎስ 5: 6).

የተወደዳችሁ ሆይ ለዚህ የተከበረ የጌታ የልደት በዓል እንኳን አደረሳችሁ። በገነት በመገኘታቸው የሚደሰቱትን ወድ ሰማዕቶቻችንን እናስታውሳለን። የቆሰሉትንም እናስታውሳለን፤ ለመፈወሳቸውም እንጸልያለን። ስለ ዓለም ሰላም እንጸልያለን። ለአገራችን ግብፅ ለእያንዳንዱ ሰው፣ ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን እና ለእያንዳንዱ አገልግሎት። አምላክ ይህንን ደስታ ለሰዎች ሁሉ እንዲልክላቸው እንጸልያለን። የቅዱስ ልደቱ መዝሙር እንደሚለው "ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ" (ሉቃስ 2 14)። ሰላምታዬና መልካም ምኞቴ ለሁላችሁ ይድረሳችሁ። በዚህ አዲስ ዓመት ውስጥ የተባረኩ ቀናትን እመኝላችኋለሁ።ይህንን ደስታና ፍቅር ለሁሉም እንዲሁም ለምትኖሩባቸው ማኅበረሰቦች በሙሉ ለማካፈል ትችሉ ዘንድ የልደት ደስታ በልባችሁ ይሙላ ። እግዚአብሔር ህይወታችሁን ይባርከው፤ የእጆቻችሁንም ሥራ ሁሉ ይባርክ። ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ዛሬም ለዘወትርም ክብርና ምስጋና ይሁን፤ አሜን።